# ምን ተማርክ/ሽ?

## ጠቃሚ ምክሩን ይማሩ

1. **ርዕሱን ተናገር/ሪ:** ልጅዎ በአጠቃላይ መፅሀፉ ስለምን እንደነበር እንዲነግራችሁ/እንድትነግራችሁ ጋብዙት/ዟት።
2. **በጣም ጠቃሚ የሆኑትን መረጃዎች ተናገር/ሪ:** ይሄ "ምኑ ይስባል" ብቻ ብሎ ከመጠየቅ ይለያል። ዋነኛው ሀሳብ ወይም ሀሳቦች ነው። ፀሀፊው ስለርዕሱ ምን ሊያስተምረን እንደፈለገ አስብ/ቢ። በርካታ ነገሮችን ሊሆን ይችላል። ልጅዎ ሀሳብን ለማሳመን ቃላትን እና ሀረጎችን እንዲጠቁም/እንድትጠቁም ጋብዙት/ዋት።
3. **ቀልድ ወይም አስደሳች እውነታን ተናገር/ሪ:** አሁን ሁለታችሁም ስለተማራችኋቸው በጣም አስደናቂ፣ አስገራሚ፣ የሚያስጠላ፣ የማይታመን፣ ያልተጠበቁ ነግሮች ተናገሩ! ይሄንን እውነታ የሚያሰዩ ቃላትና ምስሎች ፈልጉ።

**ይሄ ጠቃሚ ምክር ለምን አስፈለገ?**

ለኢ-ልቦለድ መፅሀፍት ራሳችንን "ምን ተማርን?" ብለን መጠየቅ እንችላለን። በዚህ መንገድ በአዕምሯችን መረጃ ማደራጀት እና በዋነኝነት ደግሞ ማስታወስ እንችላለን!

## ልጅዎን ይጠይቁ

*ለትናንሽ ልጆች:*

- ይህ መፅሀፍ በአጠቃላይ ስለምንድን ነው? በአብዛኛው ስለምን?
- ሳትጠብቀው/ቂው የተፈጠረ አስገራሚ ነገር ምን ነበር? ይሄንን ከመፅሀፉ የት ጋር እንደተማርክ/ሽ አሳየኝ/ዪኝ።
- ቀድሞም የምታውቀው/ቂው ነገር ምን ነበር?

*ለትላልቅ ልጆች:*

- አሁን መፅሀፉንም ጨርሰህ/ሽ የምታስበው/ቢው ምንድን ነው?
- ስለምን እንደሆነ በማሰብ፣ ፀሀፊው ስለዚህ ርዕስ ምንድን ነው ሊያስተምረን ያሰበው/ችው? እንዴት እንዳወቅህ/ሽ ንገረኝ/ሪኝ።
- ለጓደኛህ/ሽ ስለዚህ መፅሀፍ በሙሉ መናገር ብትፈልግ/ጊ ማካፈል የምትፈልገው/ጊው ዋነኛ ነገሮች ምንድን ናቸው?

## አዝናኝ ልምምድ

ልጅዎ በተጨማሪ መማር ስለሚፈልገው/ስለምትፈልገው ነገር ተነጋገሩ። ስለርዕሱ አሁን የሚያውቀውን/የምታውቀውን ነገር እና መማር የሚፈልገውን/የምትፈልገውን ነገር ዝርዝር አዘጋጁ።

ቀጥሎም ይሄንን ርዕስ ከኢንተርኔት ላይ የበለጠ ዳሰሳ አድርጉ። መረጃውችን ስታገኙ ከዝርዝሩ ላይ ልጅዎ መማር የሚፈልገውን አረጋግጡ። አዲስ ጥያቄዎችን ፃፉ።

ለመጀመር የሚከተሉት የኢንተርኔት ገፆች ጥሩ ይሆናሉ:

- www.kids.nationalgeographic.com
- www.dkfindout.com
- www.weatherwizkids.com
- www.pbslearningmedia.org